# የምፅዓቱ የምሥራች

ቅጽ 76 ቁጥር 6(906)
76 ፥3(903)

"በፍጹም ልቤ ፈለግሁህ" (መዝሙረ ዳዊት 118፡10)
"...በፊቴ የሚቆም ሰው ፈለግሁ" (ሕዝቅኤል 22፡30)

## እግዚአብሔር በፍጹም ልብ የሚፈልጉትን ሰዎች ይፈልጋል!

(በስፓርጀን እና በኮንሉን)

የዚህ እትም የምጽአቱ የምሥራች ለክርስትና እጅግ አስፈላጊ በሆኑት ሁለት ጉዳዮች፡- ፍፁም ልብና የሚያገለግሉትን በፊቱ የሚቆሙትን ለፈረሰው ቅጥር ግድ የሚላቸውን በሚመለከት ላይ ያተኩራል።

እውነተኛ ሃይማኖት በብርቱ የሚቃትት ልብና የሚቀጣጠል መንፈስን ይፈልጋል።

ወደ ተስፋ ምድር የሚጓዙ ሰዎች የተስፋ ምድራቸውን ቀንና ሌሊት በሙሉ ልብ በመፈለግ እንደሚጓዙ ይታወቃል። ክርስቲያኖችም በእውነተኛ ልብ በብርቱ ትጋት የመጨረሻ ግባቸው የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ፊት ለፊት በዙፋኑ ላይ ለማግኘት ይጓዛሉ፤ ይኖራሉ።

እግዚአብሔርን ከሰጠን ኃይልና ችሎታ በታች በማገልገል ልናስደስተው አንችልም። *"እንዲሁ ለብ ስላልክ በራድም ወይም ትኩስም ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው" ራዕይ 3፡16*

ይህ አባባል የተጠቀሰው ጌታን በሚገባው ቅናትና ትጋት ለማያገለግሉት ሁሉ እንደማስጠንቀቂያ ለማትጋትና የበለጠ በመንፈስ ለማቀጣጠል የተሰጠ ነው።

እግዚአብሔር እኛን የሚወደን በሙሉ ልቡ ስለሆነ የእኛም ምላሽ በሙሉ ልብ ባልተከፈለ ልብ መሆን ይገባዋል።

ክርስቶስ የቤተ-ክርስቲያን ባል ሲሆን ቤተክርስቲያን ሚስት ነች።እንግዲህ አንድ ባል ሚስቱን በሙሉ ልብ ካላፈቀረና ካልተሰጠ ምን እንደሚከተል እናውቃለን። ብዙ ትዳሮችና ቤተሰቦች የሚፈርሱት በተከፈለ ልብ ባልና ሚስት ኑሮን ሲገፉ ነው። ስለዚህም የባልና የሚስት ግንኙነት ፍቅር ምሳሌ የሆነው የክርስቶስና የቤተክርስቲያን (የአማኞች) ግንኙነት እንዳይፈርስ እርሱ ክርስቶስ ህይወቱን እሲኪሰጥ ድረስ የሰጠንን ፍቅር ለመጠበቅ አማኞች በሙሉ ልብ ልናፈቅረውና ልናገለግለው ይገባል።

ወንድሞችና እህቶች ሁላችንም ለክርስቶስ ብቻ ሊከፈት የሚገባውን ልባችንን ለዓለምና ለስጋችን በመክፈት የሰይጣን መጫወቻ ሆነን እንዳንወድቅ ፈጥነን ልባችንን

ለክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ እንጠብቅ እንፍቀድለት፡፡

ህይወታቸው የሚወላውል ሰዎች ከራሳቸው ይልቅ ሌሎች በቅርባቸው ያሉ ሰዎች ተስፋ የሚቆርጡባቸው ይሆናሉ፡፡ ክርስቲያኖች በድፍረት ኃጢያት ሲገዙና መሪዎች ባልተገባ ሥፍራ ሲታዩ ተከታዮቻቸው እጅግ ይጎዳሉ፤ ይሰናከላሉ፡፡ ስለዚህም በየዕለቱ ልባችንን በክርስቶስ መንፈስ በመጠበቅ ለሚመለከቱን ሁሉ መልካም ምሳሌ እንሁን፤ ፈጥነንም ንስኃ እንግባ፡፡

እግዚአብሔርና ትዕዛዛቱን የምንጠብቅ በቅድስና ብቻ ነው፡፡ ያለ ቅድስና እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻልምና፡፡ *(ወደ ዕብራውያን 12:14)*

*"ትዕዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው አወናውቃለን" (1 ዮሐንስ 2:3)*

ብዙውን ጊዜ ሰዎች ከክርስቶስ የሚለዩት ክፉ ነገር ወደልባቸው የሚገባው በምቾትና በብልጽግና እያደጉ ሲመጡ ነው፡፡ ሆኖም ግን ስደትና በክርስትና እምነት የተነሳ የሚደርሱብን ነገሮች ሁሉ እምነታችንን የሚያጠነክሩ ሆነው እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ከክርስቶስ የሚለየኝ አንዳች ነገር የለም እንላለን፡፡(ሮሜ 8:35)

የክርስቶስ ቃል ሥልጣን ስላለው ዘወትር በልባችን እናኑረው በዚያ የልብ ዕናት ይገኛልና፡፡

ሀገሮችና ሕዝቦች ከእውነት መንገድ ሲሮጡ የሚመክሩና የሚመልሱ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው፡፡

በኃጢያትና በቅድስና በእውነትና በሀሰት መካከል ልዩነት ጠፍቶ ሁሉ ወደክፋት መንገድ በሚሮጥበት በዚህ ዘመን እግዚአብሔር የእርሱን አጀንዳ የሚያስፈጽሙለትን ሰዎች ይፈልጋል፡፡

እግዚአብሔር በሕዝቅኤል ትንቢት በኩል ሰው አጣሁ ሲል በጣም ይገርማል፡፡ ቤተ መቅደሱ በሰዎች ተሞልቶ የሚያጥኑ የሚዘምሩ የሚሰግዱ እየተግተለተሉ እግዚአብሔር ሰው አጣሁ ማለቱ በትክክል የእርሱን ሀሳብ የሚያስፈጽሙ ሙሉ ልባቸውን ለእርሱ የሰጡትን ያለማግኘቱን ነው የሚያሳየን፡፡

ዛሬም በሀገራችንና በዓለም ዙሪያ የምናየው የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ብዛት የዘማሪ ብዛት ሳይሆን ለጌታ ግድ የሚላቸው ሙሉ ልባቸውን ለእርሱ የሰጡትን ያለማግኘቱ ነው፡፡

እግዚአብሔር በብዙ መቶ ሺዎች ጠላቶች የተከበበውን ጌዲዮንን ሰው እፈልጋለሁ ብሎ ጌዲዮን ማመን እስኪያቅተው ድረስ የፈለገው ፅኑ ሙሉ ልቡን ሰጥቶ እንደሚያገለግለው ስላወቀና ስላዘጋጀው ነበር (መሳፍንት 6:12) ጌዲዮን በዚያን ወቅት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በደረሰው ነገር ተስፋ ቆርጦ የእግዚአብሔርን መልአክ መልዕክት ማመን ቢሳነውም ጌታ ልቡን አይቶ ጠራው፡፡

በመጨረሻው ቀን በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ስንገኝ እግዚአብሔር ለዘመናት የልቡ የሆኑትን ጽኑ ሰዎች ምን ያህል ሲፈልግ እንደኖረ እንረዳለን፡፡ በዚህ በዘመናችን ምህረቱ የበዛ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከሚመጣው ዘላለማዊ ቁጣ ለማዳን ሲፈልግ ችላ ከማለት የበለጠ አሳዛኝ ነገር የለም፡፡

በጸሎትና በምልጃ በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖችን ማስተባበርና ማትጋት የዚህ

የተፈላጊ የባለ ጽኑ ልብ ሰዎች መለያ ምልክት ነው።

ክርስቶስ "ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል" ብሎ ስለጸሎት አስፈላጊነት ደጋግሞ ያስተማረው እየተረሳ ቤተክርስቲያን ቅድሚያ ሳትሰጥ እጅግ የሚያሳዝን የክርስትና ውድቀት ምልክት ነው።

የምጽአቱ የምሥራች የእንግሊዝኛውም ሆነ የአማርኛው እና ሌሎች ትርጉሞች በሙሉ በዚህ ታላቅና የክርስትና ተከታዮች አገልግሎት የሆነውን የጸሎት አገልግሎትን ያለማቋረጥ ያሳስባሉ።

በፈረሰው በኩል ለእግዚአብሔር ቅጥር መቆም የሚቻለው ራሱ ባዘዘው የጸሎትና የምልጃ አገልግሎት ነው። *"እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውኃ ኑ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ። ገንዘብን እንጀራ ላይደለ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ አድምጡኝ በረከትንም ብሉ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው ጆሯችሁንም አዘንብሉ ወደ እኔም ቅረቡ፤ ስሙ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች የታመነችይቱን የዳዊትን ምህረት የዘላለም ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ" (ኢሳይያስ 55፡1-3)*

## በእግዚአብሔር ቃል ስለመጸለይ

- እግዚአብሔር ምህረቱን በሁሉም ላይ ስለሚያፈስ እናመስግነው።
- እግዚአብሔር የምጽአቱ የምሥራች በኩል በዓለም ዙሪያ እንዲሰራ እንጸልይ።
- እግዚአብሔር በሙሉ ልባቸው የሚፈልጉና የሚተጉ አገልጋዮችን እንዲያበዛልን እንማጸነው።
- እግዚአብሔር በመንፈስም በአካልም መድረስ ወደሚገባን ሰዎች እንዲያደርሰን እንጠይቀው፤ *"ወደተቀደሰ ተራራዬ አመጣቸዋለሁ በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ (ኢሳይያስ 55፡7)*

## ቤተክርስቲያን የሚያስፈልጋት ድል አድራጊ ጸሎት ነው

እግዚአብሔር በዘመኑ እጅግ የሚፈልጋቸው የድል ጸሎትን የሚያውቁ ሴትና ወንድ ልጆቹን ነው። የጌታ ቤት ሥራ እየቀዘቀዘና እየተዳከመ የሚመጣው በጸሎት ከሚቃትቱ ይልቅ ብዙ የሚያወሩ፣ በጾም ጸሎት ከሚተጉ ይልቅ በምግብ ግብዣና ደስታ የሚሽቀዳደሙ ስለበዙበት ነው።

እግዚአብሔር የድል ጸሎት የገባቸውና የሚያካሂዱትን በብርቱ ይፈልጋል። በዚህ ብርቱ ጾምና ጸሎት ደህንነት ይገኛል የሚል የጌታ ትምህርት የለም። ምክንያቱም ደህንነታችንን በእምነት በጸጋው ብቻ ተቀብለናልና። (ኤፌሶን 2፡8)

ሆኖም ግን የክፉውን የሰይጣንን ሥራ በማፍረስ ብዙዎችን ከሰይጣንና ከዓለም ከሥጋ ባርነት ለማስፈታት ጾምና ጸሎት ትልቅ መሳሪያ ነው። (ማርቆስ 16፡17 ፣ ማርቆስ 9፡29 ፣ ማቴዎስ 17፡21 ፣ ሐዋሪያት 2፡1)

በአንድ ልብ በሙሉ ልብ በተጸለየ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይል ምርኮን ያመጣል፤ የታመሙትን ይፈውሳል፤ የታሰሩትን ይፈታል።

ክርስቲያኖች ከመንፈስ ቅዱስ ደግም የተወለድነው ለጸሎትና ለምልጃ አገልግሎት ነው (1 ቆሮንቶስ 1:9 ፣ ኢሳይያስ 62:5 ፣ ኤፌሶን 5:25)

እግዚአብሔር ካህናት ያደረገን ለእርሱ መንግስት ተወካዮች በመሆን በብርቱ ድል አድራጊ ጸሎት ሰይጣንና ተከታዮቹን ለመደርመስ ነው። (ራዕይ 1:6፣ 1 ጴጥሮስ 2:5)

ቤተክርስቲያን በጸሎት ኃይልን ከጌታ በመቀበል ብርቱ ፣ የገሀነም ደጆች የማይቋቋሟት ሆናለች። (ማቴዎስ 16:18)

ዛሬ ክርስቶስ በዙፋኑ ከፍታ ላይ የሚቀመጠው ቤተክርስቲያኑ በምታደርገው ድል አድራጊ ጸሎት ነው። የክርስቶስን የመሰሉ የምልጃ አገልግሎታ የፈጸመ የለም። ሰው በመሆኑ የሰውን ማንነት ሲረዳ በአምላክነቱ ደግሞ የሰውን በደልና ኃጢያት ፈፅሞ ማስወገድ ይቻለዋል።

መንፈስ ቅዱስ ይህን የመማለድ ጸሎትና ጸጋ በእኛ ውስጥ በክርስቶስ አሳድሯል (ሮሜ 8:26) በእንባ ጸሎት ከእግዚአብሔር ከአባቱ ጋር ዘወትር የሚገናኘው ክርስቶስ ለእኛ መልካም ምሳሌና መሪያችን ነው።

እግዚአብሔር የልጆቹን ጸሎት ሁል ጊዜ 7/24 ያዳምጣል። እኛ ያልተመለሰ ቢመስለንም እርሱ ሁሌ ይመልሳል።

*"የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልገው ያገኛል መዝጊያን ለሚያንኳኳ ይከፈታል" ማቴዎስ 7:8*

## *የቀድሞ (የመጀመሪያ) ፍቅራችሁን ትታችኋልን? (ራዕይ 2:2-7)*

የቀድሞውን የመጀመሪያውን ፍቅር ረስተን ከሆነ በአደጋ ላይ ነንና ራሳችንን እንመርምር። ከጸሎት ህይወት ከራቅን፣ ከምስክርነት ህይወት ከተቆጠብን፣ ቃሉን ከማጥናት ከሰነፍን ይህ በትክክል ለክርስትና አደጋ ነው።

በእውነት ይህን የተዉ ሰዎች ክርስቲያን መሆናቸው ጥያቄ ባይኖረውም ህይወታቸው ግን በጥያቄ ላይ ነው። በራድ የክርስትና ህይወት ከሰይጣን በሚላክ ፈተና፣ በዓለም ማታለልና ከስጋችን ደካማ ፍላጎት የተነሳ ይከሰታል። አልፎ አልፎ ቃሉን በማንበብ ቤተ ክርስቲያንም ለታይታ መሄድ ቢኖርም የበራድ ሕይወት ለራስም ለሌሎችም እንቅፋት የሆነ በንስኃ መስተካከል የሚገባው እርምና ስንፍና ነው።

ሰይጣን የተዘራውን የሚሰርቀው የእግዚአብሔር ሰዎችንም ወደጥፋት የሚነዳው በእንቅልፍ/በራድ/ ሕይወት ላይ ስንገኝ ነው። (ማቴዎስ 13:25) ብዙ ጊዜ በመንፈሳዊ ህይወታችን ለውድቀት የምንዳረገው ውስጣችን በጽኑ የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ስለማይሞላ ነው። "በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው" የሚለው ቃል የሚሰራው የሰይጣንን የዓለምንና የሥጋችንን ፈተና በክርስቶስ ቃልና መንፈስ ስንሞላምና ስንረታ ነው። (ያዕቆብ 1:12)

በስጋ የተራቡ ሰዎች አጥንታቸው ደርቆ እንደሚታይ ሁሉ በመንፈስ ስንደርቅም እንደዚሁ ነብሳችን የገራጣች ትሆናለች።

ስጋችን እንዳይከሳ ጠቃሚ ምግብ እንደምንመገብ ሁሉ ነፍሳችን እንዳትከሳ የእግዚአብሔርን ቃልና መንፈስ በየቀኑ መመገብ ይኖርብናል። (ማቴዎስ 4፡4) ነፍሳችን ዘላለማዊ ስለሆነች ምግብ የምታገኘው ከዘላለሙ አምላክ ብቻ ነው። ለመንፈሳዊ ምግብ ፍላጎት ስናጣ ያን ጊዜ ዓለምና ሰይጣን በሕይወታችን መንገስ ይጀምራሉ፤ ወደ ጥፋትም ይመሩናል።

ለመንፈሳዊ ውድቀት ብዙ ጊዜ ምክንያቶቹ ስውር ኃጢአትን መለማመድ ነው። ዛሬ እንደቀላል የሚሰማን ኃጢያት ነገ ልማድ ሆኖ ሊገድለን ስለሚችል ቃሉ በገለጸልን ወቅት ንስኃ በመግባት ከኃጢያታችንን እንመለስ። በዚህም የጠፋብን የቀድሞው የመጀመሪያው ፍቅር ይመለሳል።

“እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ንስኃም ግባ የቀድሞውንም ሥራህን አድርግ።” (ራዕይ 2፡5)

## ልብን ስለመመርመር

መንፈስ ቅዱስ የግለሰብም ሆነ የህብረተሰብ መንፈሳዊ መታደስና መነቃቃት ደራሲ ነው። ሰዎችን ስለኃጢያት በመውቀስ ስለክርስቶስ የመመስክርና የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያሳይ መንፈስ ቅዱስ ነው።(ዮሐንስ 16፡7) መንፈስ ቅዱስን ተሞልተው ታላላቅ የእግዚአብሔርን ስራዎች የተፈጸመባቸው ክርስቲያኖች ሁሉ በመጀመሪያ በውስጣቸው ያስቸገረን እርም በንስኃ በክርስቶስ መንፈስ ያዘጋጃሉ።

ለአንድ የእግዚአብሔር ልጅ የተገባው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መቀበያ ጸሎት በመዝሙረ ዳዊት 138፡23 ላይ ይገኛል። *“አቤቱ መርምረኝ ልቤንም እወቅ ፈትነኝ መንገዴንም እወቅ በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ የዘላለሙንም መንገድ ምራኝ”*

ራስን መመርመር እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው የማንነታችን መነሻ የሆነውን ልባችንን አእምሮአችንን በመመርመር ነው። ስሜታችንና አካባቢያችን ሊያስቱን ከእውነቱ ሊያርቁን ሲችሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ወደልባችን በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ በተመራ ጸሎት ማንነታችን በሚገባ እንድንመረምር እንድንፈትሽ ያስችለናል። በራሳችን የተሰራና ያልተረዳነውን ስህተትና ኃጢያት ሌላው የጓደኞችን የቤተሰባችን በማድረግ በማላከክ ማመካኘት የስጋ ባህሪ ነው። ሆኖም ግን የጌታ ቅዱስ መንፈስ ወደ ልባችን በቃሉ ሲዘልቅ “እኔ ነኝ በደለኛው” እንደ ዘማሪው ተስፋዬ ጋቢሶ “እኔ ነኝ ደካማው የጥፋቱ ምክንያት” እንላለን። ደቀመዛሙርቱ ከእኔነት ወጥተው ጌታኮ ነው ያሉት ያ ድንቅ መንፈሱ ወደልባቸው ዘልቆ ራሳቸውን መመርመር መመልከት በቻሉበት ሰዓት ነበር (ማቴዎስ 26፡22)

የእግዚአብሔር መልዕክት በቃሉ አማካኝነት በስብከት፣ በትንቢት፣ በመዝሙር፣ በመገለጥና በትምህርት ሲመጣልን ልባችንን ለመመርመር የተዘጋጀን ብንሆን ከብዙ ጥፋትና ውድቀት ራሳችንንም ሆነ ሌሎቹን እናድናለን። ከክርስቶስ ጋር ነን ብለን የምንመሰክር ከሆነ ቅዱስ ቃሉ በህይወታችን እያደረ ዘወትር ጨለማውን ከብርሃን በመለየት ከብርሃን ጋር ሁል ጊዜ ለመኖር ምርጫና ትጋትን እናሳያለን። *“እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት፤ ከእርሱ ጋር ህብረት አለን ብንል በጨለማ ብንመላለስ እንዋሻለን፤ እርሱ*

*በብርሃን እንዳለ ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ህብረት አለን" (1 ዮሐንስ 1:6)*

## እግዚአብሔር የጸሎት አገልጋዮችን ይፈልጋል

በትንቢተ ኤርሚያስ (5:1) ላይ እግዚአብሔር አንድ ሰው ብቻ እንኳ ጻድቅና እውነተኛ ቢያገኝ ኢየሩሳሌምን በሙሉ እንደሚያድን ይናገራል። በትንቢተ ሕዝቅኤል 22:30 ደግሞ እግዚአብሔር ለፈረሰው ቅጥር የሚቆም ሰው እንደሚፈልግ ይናገራል። *በኢሳይያስ 59:15 "እግዚአብሔርም አየ ፍርድም ስለሌለ ተከፋ ሰውም እንደሌለ አየ ወደ እርሱ የሚመልድ እንደሌለ ተረዳ"*

አንድ ሰው ብቻውን ለውጥ ሊያመጣ ይችላልን? እግዚአብሔር ምን ዓይነት ሰው ነው የሚፈልገው? እግዚአብሔር ስለሰዎች ግድ ብሎት ለእርሱ ምልጃ የሚያቀርብ በጸሎት የሚቃትት ሰው ይፈልጋል። እግዚአብሔር በዕብራውያን መልዕክት እንደተጻፈው አማላጅ አስታራቂ አስማሚ ይፈልጋል። እግዚአብሔርን ሰዎች እንዴት ሊገናኙና ምህረቱንና ይቅርታውን ሊያገኙ ይችላሉ? (ወደ እብራውያን ሰዎች 9:15) ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ/አማላጅ አምላክና ሰው ነው። በዓለማችን ታሪክ በክርስቶስ ፈለግ እግዚአብሔርንና ሰዎችን፣ ሰዎችን ከሰዎች የሚያማልዱ የሚያስታርቁ አገልጋዮች ታይተዋል ታላላቅ መፍትሄዎች አስገኝተዋል። *"እርሱ ስለበደላችን ደቀቀ ህመማችንንም ተሸከመ" (ኢሳይያስ 53:4)* የአብርሃም ታሪክም እንደዚሁ የመማለድ አገልገሎት ነበር። በአብርሃም ጸሎት ምክንያት ሎጥ ከነቤተሰቡ ከቁጣ ሲተርፉ የሎጥ ሚስት ግን ባለመታዘዝ የጠፋችው ለእኛ ከእምቢተኝነት እንድንርቅና እግዚአብሔርን እንድንታዘዝ ተጽፏል።

የመማለድ አገልግሎ የሌላው ችግርና ኃጢአት የእኔ ጉዳይ ነው ብሎና ለመፍትሄው ወደ እግዚአብሔር በጸሎት በምልጃ መቅረብ ነው። በዚህ ወቅት በኃጢያት ቀንበር ያሉ በትዳር ችግር የሚሰቃዩ በስራ ማጣት የተጎዱ በዘር ልዩነት የተገፉ፣ በጤና ማጣት የሚሰቃዩ፣ በተስፋ መቁረጥ የሚኖሩ፣ በአጠገባችን በሌላም ስፍራ ይኖራሉ። ለእነዚህ ሁሉ እግዚአብሔር በእኛ ምልጃ ጸሎት መፍትሄ ይሰጣል።

## እውነተኛ ልብ

የሰው ልብ የሚባል ጥሩ መጽሐፍ ከመካነኢየሱ መጽሀፍት መደብር በማግኘት ያነበብኩ ሲሆን ለብዙ ሰዎች በማስራጨት ትምህርቱን አካፍያለሁ። በመጀመሪያ በልብ ውስጥ ያሉ ክፉ ነገሮች በምስሎች የተገለጹ ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ሲገባ ያ ክፉ ልብ ተቀይሮ የእግዚአብሔር ማደሪያ ሆነ። ለዚህ የጥሩ እውነተኛ ልብ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይናገራል። *"በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ" (ወደ ዕብራውያን 10:22)* እውነተኛ ልብ ቅን ልብ ተብሎ በመጽሀፍ ቅዱስ ይታወቃል። ያ ቅንነት የሚገኘውም በክፍሉ እንደተገለጸው በተረዳንበት እምነት ነው። የተረዳንበት እምነት በእግዚአብሔ ቃል ያለና በልባችን የሞላ በአፋችን የሚፈስ የእውነት ቃል ነው (ሮሜ 10:17)

በትንቢተ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ኃጢአተኛ ሰዎች በአፋቸው እንደሚያከብሩት ልባቸው ግን ከእርሱ እንደራቀ የተናገረው በዚህ በዘመናችንም የሚታይ ነው። (ማቴዎስ

15:7፣ ኢሳይያስ 29:13) አብርሃም ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ የተገዛው መጀመሪያ እግዚአብሔር እውነተኛ ቅንልብ በእምነት በልቡ ስለፈጠረለት ነበር (ዘፍጥረት 15:6) ይህ በሙሉ ልብ ለእግዚአብሔር መታዘዝና ቅን ልብ ማግኘት በእግዚአብሔር ቃል በብዙ ሥፍራዎች ተጠቅሷል። *"በእግዚአብሔር ታመን በራስህ ማስተዋል አትሂድ" (ምሳሌ 3:5)* ከእረኝነት ከፍልስጤም የጦርነት አደጋ ተርፎ በድል አድራጊነት ኢየሩሳሌም የነገሰው ንጉስ ዳዊትን እግዚአብሔር ባለ ቅን ልብ ብሎታል። (1 ሳሙኤል 13:14) (ሐዋሪያት ሥራ 13:22)

በዓለማችን ታሪክ ለብዙ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ተሀድሶዎች መነቃቃቶች እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ወንድና ሴት ልጆቹ ልባቸው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተለወጠ ቅንና እውነተኛ ነበሩ። ስለዚህ እግዚአብሔር በሰዎችና በሀገሮች ላይ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ውጫዊ የልብስ ሳይሆን የውስጥ የልብ ለውጥን ይሻል፤ ያደርገውማል። *"ወደ እኔ ተመለሱ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ" (ኢዩኤል 2:13)*

## <u>መልዕክት ከአሳታሚውና ከተርጓሚው</u>

ሪክ ካርማይክል እና
ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ

## *እግዚአብሔር ልብን ሲነካ ፈውስና በረከት ይከተላል።*

የእግዚአብሔር መልዕክት በቃሉ አማካኝነት ወደ ሰዎች በደረሰ ጊዜ ሰዎች ክፉ ስራቸውን ኃጢአታቸውን በመረዳት ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ። በብሉይም ሆነ በአዲ ኪዳን እንደሚታየው የእግዚአብሔር መልዕክተኞችና አገልጋዮች ዋናው ሥራ እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክን ከኃጢአተኛ ሰዎች ጋር ማስታረቅ ማስማማት ነው።

ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲስማሙ ብዙ መልእክተኞች የተላኩ ሲሆን የመጨረሻ ዋነኛ መልዕክተኛ እራሱ አምላክና ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ወደ ዕብራውያን 1:1-3)

የምጽዓቱ የምሥራች የእንግሊዘኛው እትምም ሆነ ከሰላሣ በላ የሆኑት የትርጉም ስራዎች ዋነኛ መልዕክትም ይህ ቅዱስ እግዚአብሔርና ሰዎችን የማስታረቅ በዚህም ሰዎችን ከዘላለም ሞት ከገሀነም ማዳን ነው። ይህንን መልእክት ለሰዎች የሚያቀርቡ ደግሞ ቅን ልብ ያስፈልጋቸዋል(ሕዝቅኤል 36:26)

እግዚአብሔር የመጀመሪያ ትዕዛዛቱን በሽክላ ቀጥሎም በግራር እንጨት በታቦቱ በጽላቱ ላይ የጻፈ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን በአማኞች በክርስቲያኖች ልብ ላይ በመንፈስ ቅዱስ አትሞታል። (ወደ ዕብራውያን 8:10፣ ዮሐንስ 13:34፣ ትንቢተ ኤርሚያስ 31:33)

እግዚአብሔር ደህንነትን የሰጠን በልባችን ሀሴት በማድረግ ታላቅነቱን አዳኝነቱን ለፍጥረት ሁሉ እንድንመሰክር ሲሆን በዚህም ትልቅ ሽልማት ይጠብቀናል። (መዝሙረ ዳዊት 31:24፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 3:13፣ መዝሙረ ዳዊት 40:8)

ክርስትና የአንደበት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የልብ ጉዳይ ነውና ዘወትር በታማኝነት

*ቅዱስ ደግና ርህሩህ የዋህ ልብ ጌታ እንዲሰጠን እንማጸነው፡፡ "አቤቱ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ፣ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ" (መዝሙረ ዳዊት 51፡10)*

## ዓለም አቀፍ ዜናዎችና የጸሎት ርዕሶች

### ከእስራኤል

*ለዚህ ዘላለማዊ መልዕክት ለሚያቀርብልን ጋዜጣችሁ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ የመጨረሻው መጨረሻ ከሰይጣን ጋር ውጊያ ላይ ነንና በጸሎት ከድል አድራጊው ክርስቶስ ጋር እንድንቆም ጸሎት አድርጉልን፡፡*

### ከጃማይካ

*እግዚአብሔርን ስለእናንተ ስጦታ ላመሰግን እወዳለሁ (ፊሊጲስዮስ 1፡3) የምጽዓቱ እትም በማንበብ ዘወትር መንፈስ ይታደሳል፡፡ በዚህ ዘመን የክርስቲያኖችን ተግዳሮት የሚገልጽና መፍትሄ የሚያቀርብ ገላጭ ነው፡፡*

### ከኢትዮጵያ

*በየጊዜው ለምትልኩልኝ የምጽዓቱ የምስራች በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ለአገልግሎቱ ድጋፍ ካለችኝ ለመላክ እሞክራለሁ፡፡*

## ማሳሰቢያ

## ለአማርኛው ትርጉም አባላት

የአማርኛውን ትርጉም ለማሰራጨትና ለማሳተም እግዚአብሔር የእናንተን ትብብር ይፈልጋል፡፡ ብዙ ወገኖቻችን ይህንን እትም ለመጽሐፍ ቅዱስና ለጸሎት ህብረት ይፈልጉታል፡፡

ስለዚህ ጌታ ያሳሰባችሁን በኢትዮጵያ ብር ወይም በማንኛውም ገንዘብ ለኢትዮጵያ ተወካይ ለአልማዝ አሳየ በሚከተለው አድራሻ በመላክ የእግዚአብሔርን ስራ ተባበሩ፡፡

ለአገልግሎቱ መስፋፋትና ለብዙዎች መዳን ዋና መሳሪያ በጸሎታችሁ ደግፉን፡፡

የምጽዓቱ የምሥራች ዓለም አቀፍ የወንጌል መነቃቃት አገልግሎት

አሳታሚ፡- ሪክ ካርማይክል
ትርጉም፡- ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴመካሻ
በኢትዮጵያ ተወካይ፡- አልማዝ አሳየ
የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ
*ኮምፒተርና ዲዛይን*
*አቤኔዘር የፅህፈት ሥራ*
*መካኒሳ አዲስ አበባ*
ኢትዮጵያ